የረቡዕ መስከረም 4 1998 ዓም ( ሴፕቴምበር 14 2003)

## የፍኖተ ዴሞክራሲ ሐተታ

## የአፈናን ኃይል ማጠናከር፥ ከሕዝብ ቁጣ አያድንም

ሰው ሲጨንቀው ሰማይ ሊቧጥጥ ይጥራል እንደሚባለው፥ ሰሞኑን፥ መለስ ዜናዊ በሕዝብ ላይ ያለውን ፍራቻና ጥላቻ በይበልጥ የሚያጋልጠውን ተግባር ፈፅሟል:: የቤተ መንግሥቱን ጥበቃ በይበልጥ ለማጠናከር እንዲያስችለው፥ ሁለት ሻለቃ ጦር በተጨማሪ እንዲታከል አዟል:: የአዲስ አበባን ከተማ የፀጥታ መዋቅርና ዕዝ በእርሱ ስር እንዲሆን እንደገና ወስኗል:: የሀገሪቱ የፀጥታና የደኅንነት ሠራተኞችም የሦስት ቀናት ስብሰባ አካሂደው፥ ለተጨማሪ ግዳጅና ግድያ እንዲዘጋጁ ልዩ መመሪያና ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል:: መለስና ጓደኞቹ የሕዝቡ እንቅስቃሴ በይበልጥ እያሰጋቸው በመሄዱ፥ የሕዝቡን ቁጣ የተከላከሉ መስሏቸው፥ቤተ መንግሥታቸውን በልዩ ቅልብ ሠራዊት እያስከበቡ ናቸው:: የአግአዚ ክ/ጦር ቁጥርም በየከተሞቹ ከፍ ብሏል:: ይህ ጨፍጫፊ ክፍለ ጦር፥ የፌዴራል ፖሊስና የደኅንነት ኃይሎች ትብብርና ዕገዛ እንዲያገኝ ልዩ መመሪያ ወርዶለታል:: ይህ ሁሉ የፀጥታና የጨፍጫፊ ኃይል የተማከለው፥ የመለስ ዜናዊን የቀጥታ ትዕዛዝ ርምጃ በተቻለ ፍጥነት እንዲያከናውን ሆኖ ነው::

ይህ ሁሉ የፈጥኖ ደራሽ አፋኝ ኃይልና የፀጥታ ዝግጅትና እንደገና መዋቀር፥ የሀገሪቱን ዳር-ድንበር ለመጠበቅ ሳይሆን፥ ወይም ደግሞ የኢትዮጵያን ብሔራዊ የመከላከያ ሠራዊት ለማጠንከር ሳይሆን፥ የአንድን ዘረኛ ሥርዓት አራማጆች ዕድሜ ለማራዘም ብቻ ለመሆኑ ብዙ ትንታኔ የሚያስፈልገው አይደለም:: በፀጥታ ኃይል ተከብቦ የሕዝብን ቁጣ መከላከል የሚቻል ቢሆን ኖሮ፤ የኢራኑን ሟች ሻህን ሥርዓት፥ ሳቫክ የተሰኘው አስፈሪውና ኃይለኛው የስለላ መዋቅር ከሕዝቡ ቁጣ ሊያድነው በቻለ ነበር:: የደርግም ሥርዓት በአፋኝ ተቋሙ ከውድቀቱ ባመለጠ ነበር:: ያ ግን አልሆነም:: ይህንን አስመልክቶ የአያሌ አምባገነኖችን ሥርዓት ለመጠበቅ ሲባል ብቻ የተደራጁትን የቤተመንግሥት የሠራዊት ብዛትና የተዋቀሩትንም የስለላ መረቦች መጥቀስ ይቻላል:: በዚህ ላይ ብዙ ማለቱን ግን ለጊዜው እናልፈዋለን:: ለማለት የምንፈልገው ግን አንድ ሀቅ አለ:: በዓለም ያሉት የስለላ ድርጅቶችና መዋቅሮች፥ የደህንነት ሠራተኞችም ይሁኑ የኢንተሊጀስ ጠበብቶች ቢጠራቀሙ፥ ቢተባበሩ፥ ቢያድሙ -ቢኅነጉኑ፥ መለስ ዜናዊንና ግብረ-አበሮቹን ከኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጣና ቅጣት የሚያድኑት አይሆኑም:: የዘረኞች መንጋ ቢተባበር፥ ጨፍጫፊው የአጋዚ ክፍለ ጦር ቢጠናከር፥ የቤተ መንግሥቱ ጠባቂ ብርጌድ ጦር በዘመናዊ መሳሪያ ቢታጠቅ፥ የፌዴራል ፖሊስ ቢንጋጋ፥ ምድረ ሰላይ ቢጠራቀም፥የዘረኛውን ሥርዓት፥ ተከላክሎ ሊያቆየው፥ ሊያድነው፥ በመጨረሻም ሊጋፈጥለት ከቶ አይችልም:: ይህ ሀቅ በአፄውም ሥርዓት ሆነ በመንግሥቱ ኃይለማርያም አገዛዝ የተመሰከረ ሀቅ ነው:: የወያኔ ዘረኛ ሥርዓትም ዕጣ ፈንታና አስከፊ መጨረሻ ከዚህ ታሪካዊ

ሀቅ የተለይ ሊሆን አይችልም። በኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጣና የፍርድ ማዕበል ተጠራርጎ ይጠፋል።

ይህን መሠረታዊና ታሪካዊ እውነታ መምጣቱ የማይቀር መሆኑን ከተረዳን ዘንዳ፥ የሕዝቡን ትግል አፋፍሞ ተጨባጭ ውጤት ማስመዝግ አማራጭ አይኖረውም። ፥ ከሕዝብ ጎን ሆኖ፥ መስዋዕት እየከፈሉ መታገልና ማታገል ያስፈልጋል። ትግል ያለመስዋዕት፥ ስርየት ያለደም፥ ውጤት ያለተግባር ጭራሽ የሚታሰብ ነገር አይደለም። የተቃዋሚው ኃይል ተጨባጭ ውጤት ሊያስመዘግብ በሚችል ዒላማ ላይ ብቻ በማነጣጠር ጠንካራ ኅብረቱን መስርቶ መታገል፥ ይዋል ይደር የሚባልለት የትግል አጀንዳ ወይም ዕቅድ ሊሆን አይችልም። በዕርግጥ የወያኔን የዕለት ተዕለት ወንጀልና መሰሪ ከፋፋይ ምሥጢር እየተከታተሉ ማጋለጥ አስፈላጊ ቢሆንም፥ የጠቅላላው ትግል አትኩሮት፥ ይዘትና ሂደት ግን በዚህ ብቻ ሊወስን አይገባውም። የተቃዋሚው ጎራ የትግል ዕቅድ፥ ተጨባጭ ውጤት ሊያስገኝ በሚችል የቅደም ተከተል የተግባር ዘርፍ የተጀበ ከሆነ፥ በአጭር ጊዜ ውስጥ ውጤት ማስመዝገቡ አያጠራጥርም። የተቃዋሚው ጎራ የትግል አልፋና ኦሚጋ፥ ዘወትር ወያኔን በማጋለጥ፥ በማውገዝ፥ እንዲሁም በመክሰስ ላይ ብቻ ተወስኖ ሊቀር አይገባውም። የወያኔን ሰብዕና ባህርይና ተግባር ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በሚገባ ስለሚያውቀው፥ ስለ ወያኔ ማንነት መግለጫ ማውጣት፥ ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግ፥ ለምዕራቡ ዓለም የአቤቱታ ደብዳቤ ማቅረብ፥ የሚፈለገውን ውጤት እንዳላስመዘገበ፥ አሁን ያለው ሁኔታ ቁልጭ አድርጎ ያሳያል። በውጤት ላይ ብቻ ያተኮረ ትግል ማድርግ ቢያንስ በአሁኑ ወቅት ሦስት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል።

ሀ) ከሁሉ በላይ የሕዝቡን አመፅ የበለጠ ያፋፍመዋል። ሁሉም ዜጋ ለለውጥ መምጣት ተስፋው ይጨምራል ይነቃቃል። አይተነው ጊዜ ወዳደላበት በሚል ሥነ አዕምሮ የተሸበበውን መሀል ሰፋሪና እበላ ባዩ ክፍል፥ ወደ ትግሉ ጎራ የመቀላቀል ፍላጎቱ ይጨምራል። የኃይል አሰላለፉን ጥንካሬና አያያዝ አይቶ የድል አጥቢያ አርበኛ ለመሆን ይሽቀዳደማል። በዕርግጥ ይህ ክስተት፥ ለትግሉ ጥሩ ይሆናል። ለምን ቢባል፥የወያኔን ጎራ እያመነመነው የተቃዋሚውን ጎራ ስለሚያዳብረው ነው።

ለ) የእነ መለስ ዜናዊ ጎራ የመፈረካከስ ፍጥነቱ እየጨመረ ይሄዳል። ይህ እየተከሰተ በመጣ ቁጥር ደግሞ፥ የመከላካያ ሠራዊቱ፥ የፀጥታው ክፍሉና የድኅንነቱ ሠራተኛ ከወያኔ ውድቀት በኋላ ለምትመሠረተዋ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ አገልግሎቱን ለማበርከት ለመዘጋጀት ዕድል ያገኛል። በዕርግጥም የበለጠ ዕድሉ ይከፈትለታል። በመሠረቱ፥ በየሞያው የሠለጠነው ዜጋ ሁሉ፥ የተደራጀውና የተማረው ሕዝቡን ለማገልገል እንደመሆኑ፥ የአምባገነን ሥርዓት ወድቆ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሲተካ ፥ሁሉም በየክህሎቱ ሀገሩንና ሕዝቡን የማያገለግልበት፥ ሀገሩንም የማይጠቅምበት አንዳችም ምክንያት አይኖርም። የነገዋ ኢትዮጵያ፥ በየሙያ መስኩ የሰለጠነና የተማረ የሰው ኃይል ጉልበት ከመቸውም ጊዜ በበለጠ በእጅጉ ያስፈልጋታል።

ሐ) ዛሬ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ላይ ትክክለኛ ፖሊሲና ቁርጠኛ ዉሳኔ ለመውሰድ የተቸገረው የዓለም አቀፍ ኅብረተሰብና የምዕራቡ ዓለም፥ ወሳኝና የማያሻማ ፖሊሲ ለመንደፍና በተግባር ለመተርጎም እድል ያገኛል። ዕርግጥ ምዕራቡ ዓለም፥ምን ጊዜም ቢሆን ከመለስ ዜናዊ የተሻለ ታማኝ አገልጋይ እንደማያገኝ ቢረዳውም፥ ይህንን በሕዝብ አንቅሮ የተተፋን የገዥ ቡድን እስከ መጨረሻው አቅፎ ደግፎ እንደማያቆየው ደግሞ ይገነዘባል። በመሆኑም፥ በኢትዮጵያ ላይ ያለውን ፖሊሲውን ለመለውጥ የሚያስችለውን ማጠየቂያ ለማግኘት፥ የተቃዋሚውን ጎራ ውጤት ማስመዝገብ በአንክሮ ይጠብቀዋል። ለዚህ መድኅኒቱ ታዲያ የተጨበጠ የትግል ውጤት አስመዝግቦ መገኘት ይሆናል።

አሁን ሁለት ክስተቶች በይበልጥ ጎልተው ይታያሉ።

የመጀመሪያው፥ ዛሬም እንደ ትላንቱ ከገባንበት አዙሪት መውጣት አለመቻላችን ነው። የጋራ የሆነ ብሔራዊ ዕቅድና የራዕይ ዕጥረት አለብን። ሁሉም በየፊናው የየፓርቲውን ፕሮግራሙን ጽፎ ቢመጣ፥ የሀገሪቱን የጋራ ብሔራዊ ራዕይና ሀገራዊ ፖሊሲ ነድፏል ማለት አይደለም። ሁሉም የተቃዋሚ ጎራ ሌላው ቢቀር፥ በትግሉ ሂደት ወቅት አብሮ ሊያታግለውና ሊያሰባስበው የሚያስችለው የጋራ የትግል ዕቅድ ሊኖረው ይገባል። በዚህ የትግል ውጥን ዙሪያ ተሰባስቦ ወያኔን ማስጨነቅ ካልቻለ፥ የወያኔን ዕድሜ ከማስቀጠል ያለፈ ውጤት ማስመዝገብ አይቻልም።

ሁለተኛው፥ የሀገሪቱ ዕድልም ሆነ የትግሉ ዕጣ ፈንታ ከመስቀለኛ መንገድ ላይ መድረሱ ይመስለናል። ከዚህ ሁኔታ ልንወጣ የምንችለው፥ ያው ዞሮ ዞሮ እኛው ራሳችን የሀገራችንና የራሳችን የወደፊት ዕድል መወሰን ከሚያስችለን ደረጃ ደርሰን ስንገኝ ብቻ ነው። የአሁኑ ሁኔታ በትክክል ሊያስረዳን ከቻለ፥ እዚያ ደረጃ ደርሰናል ብለን እራሳችንን ማታለል አንችልም። የራሳችንን የቤት ሥራ መጀመሪያ ሰርተን ሳንገኝ፥ የውጭ መንግሥታትም ሆኑ ዓለም አቀፍ ኅብረተስብ በዘለቄታ መልኩ የኛን ችግር ያስወግዱልናል ብለን ማመን ቀርቶ መመኘት እንኳን አይገባንም። በመሆኑም፥ ከገባንበት አዙሪት ለመውጣትም ሆነ፥ ከደረስንበት መንታ መንገድ ለማለፍ፥ቢያንስ የሚከተሉትን ተግባራት በቅደም ተከተል ማከናውን አለብን። ይህም ተጨባጩን የወቅቱ ሁኔታ መሠረት ያደረገ ወሳኝና ቁርጠኛ አቋም መውሰድ ይገባል ማለታችን ነው።

1) በወያኔ ድፍረትና ዝርፊያ የተነጠቀውን የሕዝብ ድምፅ ለማስመለስ መቻል። ይህ ሊሆን የሚችለውም፡ ሁሉም የፖለቲካ ድርጅት በወያኔ ፓርላማ ላለመግባት በመወሰን ብቻ ነው።

2) መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በግንቦቱ ምርጫ ድምፁን የሰጠው፥ ለተቃዋሚ ድርጅቶች እንጅ ለወያኔ ቡድኖች ባለመሆኑ፥ ይህንን ህገ ወጥ

ሥርዓት፥ ይህን በሕዝበ ውሳኔ የተወገደ፥ ነገር ግን በአሻፈረኝነት በሥልጣኑ ለመቆየት የወሰነን የገዥ ቡድን ፥ በሕዝባዊ ሰላመዊ አመፅ ከማስወገድ ሌላ አማራጭ አለመኖሩን መረዳትና ለዚህም አሰፈላጊውን የትግል ስልት መንደፍ ያስፈልጋል። ይህ ደግሞ የማንኛቸውም የፖለቲካ ድርጅቶች ውሳኔ ወይም ፍላጎት ሳይሆን ፥ ዛሬ አልገዛም ብሎ መስዋዕት እየከፈለ የሚታገለው የመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁርጠኛ ውሳኔ ነው። የተቃዋሚው ጎራ፥ይህንን ውሳኔ የማክበር ግዴታ አለበት።

3) የተቃዋሚው ጎራ ዘላቂ ወዳጁና ወገኑ የመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ መሆኑ መቸም የሚያከራክር አይደለም። የኢትዮጵያን ሕዝብ ወገን-ወዳጅ ያደረገ ትግልም ሆነ ታጋይ ደግሞ፥ የማታ-ማታ በአቸናፊነት እንደሚወጣ በታሪክ የተረጋገጠ ዕውነታ ነው። በዚህ መሠረታዊ ሀቅ መስማማት ከተቻለ፥ ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት፥ አሁን በምንገኝበት መስቀለኛ መንገድ ላይ፥ ታሪካዊና ቁርጠኛ ውሳኔ መውሰድ ይጠበቅበታል። ከሁሉ በላይ ግን ኢትዮጵያውያን የፖሊቲካ ድርጅት መሪዎች፥ ብኩርናቸውን በጭብጥ ጥሬ እንዳይለውጡ አይገባቸውም። ሥልጣን ሰጭና ነሽ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ መሆኑን አውቀው የሕዝቡን ፈቃድ፥ ውሳኔና ጥቅም ብቻ ማክበር ግዴታቸው ነው። የሕዝብን ድምፅ ነጥቆ በተቋቋመ ፓርላማ ውስጥ መግባት የእነርሱ ቦታና ተልዕኮ አይሆንም። ታሪክ እየሰሩ የሕዝብ ወገንነትን እያስመሰከሩ መታገል፥ ኢትዮጵያ ሀገራችንን አሁን ካለችበት መከራ ማዳን ብቻ ሳይሆን፥ ለተተኪውም ትውልድ አርዓያ መሆንም ጭምር ይመስለናል። የኢትዮጵያን ዘላቂ ጥቅም፥ ሰላምና መረጋጋት፥ ልማትና ዕድገት ለማስገኘት ከሕዝብ ትግል ጎን መቆም እንጅ፥ በወያኔ መጫወቻ ፋይዳ ቢስ ፓርላማ መግባት ሊሆን አይችልም።

በአሁኑ ወቅት ሁለት ተፃራሪ ኃይሎች ተፋጥጠው ይገኛሉ። በአንድ በኩል፥ ለአለፉት አስራ አራት ዓመታት ኢትዮጵያንና ዜጎቿን በስልት እያጠፋ፥ ሀብቷን እየዘረፈ ያለ ዘረኛ ሥርዓት ሲሆን፥ በሌላ በኩል ደግሞ ይህንን ሥርዓት አንቅሮ በመትፋትና አልገዛም ባይነቱን በመስዋዕት እያስመሰከረ የሚታገለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው። ይህን የሕዝብ ትግል ለማኮላሸትና ቁጣውንም ለመከላከል፥ መለስ ዜናዊና ግብረ-አበሮቹ፥ የፀጥታውን፥ የአፋኝ ቡድኑንና የጨፍጫፊ ሠራዊታቸውን በይበልጥ እያጠናከሩና እያስታጠቁ ይገኛሉ። ዓላማቸውም ግለፅ ነው። የተቃዋሚ ድርጅቶችን ለማስፈራራትና ለመከፋፈል፥ የሕዝቡን ቆራጥ ትግል ለማዳከምና ብሎም አሁን ከሚያስፈራቸው የሕዝብ ቁጣ ጊዚያዊም ቢሆን ፋታ ለማግኘት ነው። ይህ ሁሉ ሽር ጉድ ግን ከመጨረሻው የሕዝብ ቁጣና ፍርድ ሊያድናቸው አይችልም። የሠራዊት ብዛት፥ የፀጥታ ጋጋታና የአፋኝ ቡድን መርመስመስ፥ የአግዓዚ ጭፍጨፋ፥ የፌዴራል ፖሊስ ውጣ ውረድ፥ የኢትዮጵያን ሕዝብ ትግል አያቸንፈውም። በዚህ ፈታኝ ታሪካዊ ወቅት፥ከሕዝብ ጎን ቆሞ መታገልና ማታገል የተቃዋሚው ጎራ ብሔራዊ ተልዕኮ መሆን ስለአለበትና ድል ካመለጠችም መመለሻ ጊዜዋ የራቀ ሊሆን ስለሚችል፥ ይህንን መልካም

**የታሪክ አጋጣሚ ተቃዋሚ ኃይሉ ሁሉ እንዲጠቀምበትና ወሳኝ አቋም እንዲወስድ የመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ድምፅ ጥሪውን ያስተላልፋል**!!